# ዕቴ

ወንጂ መተሃራ _ድሬና ቢሸፍቱ
ባህርዳርና አዲስ _ በየ ወይንቤቱ
አሰበ ተፈሪ_ አቃቂ በሰቃ
ቍርር ባለው ሰፈር_ ሌት በጠፍ ጨረቃ
ዕምቡጥሽ በለጋው_ በጧት መቀሰፉ
ሞተሽ ለማን ነበር_ አበባው መርገፉ?
በማይነጋ ሌሊት_ በረዥሙ አልመሽ
የማረተ ባህል _አፀዳለሁ ብለሽ
የማይድን በሽታ_ልታድኚ አክመሽ
የማያፈራ ተክል _አብዮት ኮትኩተሽ
ለራስሽ ሳትሆኚ_ ለሰው መብት ቆመሽ
በለውጥ ማዕበል_ ባመፅ ጎርፍ ታጥበሽ
አጥንትሽ ሲለቀም_ ያፅምሽ ስብርባሪ
ለማን ነበር ሞትሽ?_ ዕቴ ተናገሪ።
ተወግረሽ ተገርፈሽ _ አጥቅ አጥቅሽ ተቆርጦ
በስሪንጅ ደምሽ _በቂምሽ ተመጦ
ዐይንሽ _ ተጎልጉሎ
ጥፍርሽ ተነቃቅሎ
አካልሽ በፈላ _ዘይት ተቀቅሎ
በብልትሽ _ ዱላ .......
ግፍ ተፈፅሞበት _ ሌላም ብዙ ሌላ
እጅ እግርሽ ተሰብሮ _ በወፌ ይላላ
ሰውነትሽ ፈርሶ _ አፅምሽ ሲሰበሰብ
ለባከነው ጥይት _ለሞትሽበት ሰበብ
ዕዳሽን ሲከፍል _ ዕሬሳሽ ተሽጦ
ሀዘንሽ በዘፈን _ ሙሾው ተለውጦ
ዕለቅሶው ሽብሸባ _ ዋይታው እስክስታ
ይህ ነበር ያንቺ ሥርግ _የታሪክ ተውስታ።
አንቺስ ዕቴ _ እመቤት
አሲምባና _ ፀለምት
ውቅሮና _ ነበለት
አበርገሌ _ ብዘት
አዲሮብ _ አቀበት
ዳሆጭና _ ጓህላ

ማይፀምሪ _ሳህላ

ወልቃይት_ መዘጋ

መልዛ _ቆላ ደጋ

ጃዌና መተከል_ ቴወድሮስ ከተማ

በጠራራ ፀሐይ _ሌሊት መጨለማ

ተንከራትቶ አካልሽ_ ሜዳ የቀረሽው

ላንድ ክንድ ጉድጓድ _ለቀብር ያልበቃሽው

አፅምሽ ተልከስክሶ _ወድቆ በርሃ ላይ

ሌሊት ሌሊት ውርጬ _ቀን ሲቀቃው ፀሐይ

ሰቃይ እንግልቱ _ለማን ነበር ሞቱ

ህይዎት የከፈልሽው _ መስዋዕትነቱ

ሞትሽ ለማን ነበር _ ድል መቀዳጀቱ

ለውጥ አብሳሪው ትግልሽ _ትንሳዔ ብስራቱ

አበባሽ መርገፉ _ ጠውልጎ መሞቱ

በጧት የተቀሰፍሽ _ ለማን ነበር

# ዕቱ?

አንቺስ ያገር ቤቷ _ከልታማዋ እህቴ

ያንስታይ እያታ _ ብሩህ መስታዎቴ

አረሙ ጉልጉሎው _ ወፍጮውና መጁ

ማብሰል መቀቀሉ _ የሙቀጫ ልጁ

ቤት ማበጃጀቱ _ ፈትልና ስፌቱ

ውሃ በማድጋ _ ከወንዝ መቅዳቱ

ከርግዝና በላይ _ልጅ አዝሎ በጀርባ

ተውቦ መታየት _ቁንጅና ደርባባ

አለ ዕድሜ ጋብቻ_ ግፉ የበደለሽ

ከድርብ ጭቆና _ ነፃ እወጣ ብለሽ

ነገን ተስፋ _አድርገሽ

የመከነ _ ተስፋሽ

የቀረ ተቋጥሮ _ ህልምሽ ሳይፈታ

ድንጋይ ተንተርሶ _አፈር ውስጥ ምኝታ

የዕድሜ ድህነቱ _መስዋዕትነቱ

ሞትሽ ለማን ነበር? _ልጠይቅሽ

# ዕቱ?

የካቲት 1998

abraham beyenne